ቀን፡- 11/06/2015 ዓ.ም

ለአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት

ባህር ዳር

ጉዳዩ፡- የአብክመ የመምህራን የመብት ጥያቄዎችን ይመለከታል፦

እኛ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስተዳደር ስር የምንገኝ መምህራን ህብረት መስርተን ህገ መንግስታዊ በሆነ መንገድ የመብት ጥሰቶችን ለመከላል የተደራጀን ሲሆን እኛ የአማራ ክልል መምህራን ዘርፈ ብዙ ጣያቄዎች ቢኖሩንም እስከ አሁን ክልላዊና ሀገራዊ የእርስ በእርስ ጦርነትና ኮረና በመሳሰሉት ወቅታዊ ችግሮች ምክንያት ጥቃቄዎችን ሳናቀርብ የቆየን ቢሆንም አሁን የኑሮ ዉድነት ከኮረናና ከጦርነት የበለጠ የእግር እሳት ስለሆነብንና መንግስት የመምህራንን ጉዳይ ገርባዉን እየሰጠ ስለሆነ ጥያቄዎችን ለማቅረብ ተገደናል ።ስለሆነም ክልሉ በአስቸኳይ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ እንድሰጡን እንጠይቃለን፦

1. እኛ የአማራ ክልል መምህራን በዱር በጫካዉ ጣሻ ተራራዉ ሳይበግረን በረሀዉን አቋርጠን ሀገርን ለማስቀጠል እንደሻማ ከመቅለጥም ባሻገር ሌት ከቀን ከተናዳፊ ነፍሳትን መከላከያ እንኳን ታሳቢ ሳይደረግልን ሀገርን ለማስቀጠል በመስራታችን ደስተኞች ብንሆንም ግን በአሁኑ ሰአት ከወር ገቢ በላይ የወር ዉጭ እያወጣን በአስማት እየኖርን እንደሆነ ክልሉ ይረዳል ለጤናዉ ዱዩቲ ለብድርናዉ ሴፍትኔት የኑሮ ማዳጎሻ ሁኖ ሲያገለግል እኛ ግን የበይ ተመልካች ሁነን ሳለኝ መንግስት መምህራን ይህንን የአሰቃቂ የኑሮ ሂደት መፍትሔ እንድሰጠዉ እንጠያቃለን።

2. በግል ተምረዉ የትምህርት መሻሻልን በተመለከተ የክልሉ መንግስት በሰጠዉ አቅጣጫ መሰረት የያዙ ወረዳዎችን እያመሰገን ነገር ግን በጀት የሚል ስበብ በበጀቱ ሰኔን ጠብቆ የበጀት ማወራረጃ የሚያደርጉ ወረዳዎች እንዳሉ ይታወቃል ስለዚህ በግል ተምሮ

የመንግስትን ወጭ መጋራት በማድረጋችን መመስገን ሲገባን አለመያዙ ቢያሳዝነንም ክልሉ በሁሉም ከተማ አስተዳደሮችና ወረዳዎች ተመሳሳይ አፈጻጸም እንድኖርና እንድያዝልን በጥብቅ እንጠያቃለን ።

3. የጥያቄ ቁጥር 1 ችግሩ እንዳለ እየታወቀ የመኖሪያ ቤት ስፋት በሪጂዮፖሊታን ከተሞች 150 ካሬ በመካከለኛን አነስተኛ ከተሞች 200 ካሬ በመሪ ማአጋጃ ቤት እና በታዳጊ ከተሞች ደግሞ 250 ካሬ ድረስ ስፋት ያለዉ ቦታ ሊሰጥ ይችላል ይላል መመሪያ ቁጥር 1/2012 ዓ.ም አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተቀመጠ ሲሆን አመራሮች እስከ የሚለዉን ክፍተት በመጠቀም በሪጂዮፖሊታን ከተሞች 100 ካሬ በመካከለኛን አነስተኛ ከተሞች 150 ካሬ በመሪ ማዘጋጃ ቤት እና በታዳጊ ከተሞች ደግሞ 200 ካሬ እየተሠጠ ስለሆነ መመሪዎ ባስቀመጠዉ ጣሪያ መሰረት መመሪያ ተግባራዊ እንድደረግ በጥብቅ እንጠይቃለን።

4. የዝክረ-ህግ (ደንብ ቁ-150/2009 ዓ.ም) እስከ 2012 ዓም የሚጠናቀቅ ቢሆንም ከደንቡ አላማ አንፃር ሁሉንም መምህራን ተጠቃሚ ያደርጋል ተብሎ ቢታሰብም ሳያደርግ በመቅረቱ ምክንያት ደንቡ መራዘሙን የአ.ብ.ክ.መ ርእሰ መስተዳድር ፅ/ቤት በቁጥር አብክ 11/800/መ/ዘ/-2-24 በቀን 24/03/2011 በተፃፈ ደብዳቤ ተገልፃል። ጊዜዉ አልቋል የሚለዉ መልስ ህግን የሚጣረስ ስለሆነ ተቀባነት የለዉም ከርእሰ መስተዳደሩ መልስ ተሰጥቷል በጀትም አንለቅም የሚል ከህግ ዉጭ የሆነ መልስ ስለተሰጠን አናስተናግድም የሚል መልስ ስለተሰጠን ህጉ እንድከበር በጥብቅ እንጠይቃለን ።

5. የደሴ ከተማ ትምህርት መምሪያና መምህራን ማህበር የዝክረ-ህግ(ደንብ ቁ-150/2009 ዓ.ም) መመሪያ በተሰጣቸዉ ስልጣን መሰረት የመመሪያዉን ተግባራዊነቱን በመገምገም እንደተገበር እንድያደሩጉና እንድከታተሉ የከተማ አስተዳደሩ ሁለቱንም አካላት መሳተፍ አለመቻላቸዉ የመልካም አስተዳደር ችግር ስለፈጠረብን ስለአተገባበሩ የክልሉ ምክር ቤት ምርመራ እድርጎ አሰራሩን በማጤን አስቸኳይ መልስ እንድሰጠን እንጠይቃለን።

6. የካሳ ክፍያን በተመለከተ የዝክረ-ህግ (ደንብ ቁ-150/2009 ዓ.ም) አንቀጽ 6 ንቁስ አንቀጽ 7 መሰረት የካሳዉ ክፍያን ሙሉ በሙሉ በመንግስት የሚሸፈን መሆኑ በግልፅ የተቀመጠ ሲሆን ከተማ አስተዳደሩ የካሳ ክፍያ ገቢ እንድሆንለት መጠየቅ ያለበት የየወረዳዉና ትምህርት መምሪያወች ክልሉን መሆን ሲገባዉ እኛን መጠየቃቸዉ ስህተት ሁኖ ሳል መንግስት እንጅ እኛ እንደምንከፍል ሳናዉቅ ቦታዉን ለመስጠት 99781 ብር ከአንድ መምህር እንድከፍል ይህንን ካለከፈለ የቦታ ባለቤት እንደማይሆን የከተማ አስተዳደሮችና ወረዳዎች የወሰነ በመሆኑ ቦታዉን ላለማጣት 32 ሺ ብሩን ለመክፍል አብቁተ እዳ ስለነበረብን ሌላ አማራጭ ስለሌለን አራጣ ገብተን ብሩን በመክፈላችን አደጋ ላይ ስለሆን በአስቸኳይ መለልስ እንድሰጠን እንገልፃለን።

7. አብክመ ትም/ቢሮ በ2012 ዓም ለ524 መምህራን የካሳ ክፍያ የከፈለ ሲሆን ከተማ አስተዳደሩ መሬት ማዘጋጀት ባለመቻሉ ምክንያት የዋጋ ግሽበት በመፈጠሩ የተከፈለዉ በጀት ለ524 መምህራን የማይሸፍን በመሆኑ የችግሩ ተጠያቂ ከተማ አስተዳደሩ ሰለሆነ በየትኛዉም የህግ አግባብ ችግሩን መፍታት ያለበት ከተማ አስተዳደሩ በመሆኑ በጀቱን የመሸፈን ግደታ ስላለበት እንድሸፍን ድምፅ እንድትሆኑን እንጠይቃለን።

8. በካሳ ክፍያው ሒደት ከሚሰጠን የመኖሪያ ቤት ይዞታ ውጭ ለሌሎች ማለትም ለመሰረተ ልማት ለተለያዩ ተቋማት ተብሎ የተጨመረው የካሳ ክፍያ በከተማ አስተዳደሩ መሸፈን የሚገባው በክልሉ መንግስት ወይም በእኛ እንዲሸፈን መደረጉ አግባብነት የሌለው መሆኑን እንገልፃለን ማለትም ለኛ የሚሰጠን 100 ካሬ ሁኖ ሳል እንድንከፍል የተገደድነዉ 143 ካሬ መሆኑ ክልሉ ለከተማ አስተዳደሩ ምክር ቤት አቅጣጫ እንድሰጥልን እንጠያቃለን

9. የቦታዉ አሰጣጥ ቅደም ተከተልን በመመሪያዉና ህጉ መሰረት በፐርሰንታችን መሰጠት ሲገባዉ ከተማዎችና በረዳዎች በፈለጉት መንገድ እየሰጡ ስለሆነ ክልሉ አቅጣጫ እንድሰጥልን እንጠይቃለን ።

10. ክልሉ የፆጥታ ችግር አለብን ሲል በጠየቀው ድጋፍ መሰረት ከእጅ ወደ አፍ የሆነውን ኑሮ ተጋፍጠን የተጠየቅነውን የወር ደመወዛችንን የተጎዳነዉ እኛዉ የወር ደመወዝ የለገስነዉ እኛዉ የተሰደድነዉ እኛዉ ከመሆናችን በተጨማሪም ትርፍ ጊዜአችንን እሁድና ቅዳሜን

መስዋእትነት አድርገን መስራታችን ይታወቃል። ነገር ግን ምንም አይነት ምስጋና ሳይለገስልን መቅረቱ ቅሬታን የፈጠረብን ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም የመምህሩን አቅም በፍፁም ያላገናዘበና ሆን ተብሎ ለመጉዳት የታሳበ እስከሚመስል ድረስ ችግሩን ለመረዳት ያወያየንም ሆነ ያሰበ አካል ባለመኖሩ አሳዝኖናል። በዚህ ሰዓት የካሳ ክፍያ መክፈል አለባችሁ የሚለው ጥያቄ አግባብነት የሌለውና ጊዜን ያላገናዘበ ከመሆኑ ባሻገር ከህግ ጋር የሚጣረስ ስለሆነ ባስቸኳይ የካሳ ክፍያ እንድከፈለን እንዲሰጠን እንጠይቃለን።

11. ዉዝፍ የ9 ወር JEG ጉዳይን በተመለከተ መንግስት አካላት በተጻፈ ደብዳቤ እንደሚከፈል የተገለጸ ስለሆነ እስከ አሁን ድረስ ብሩን አለመዉሰዳችን እየታወቀ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴሩ እንደተከፈለ የተናገሩ ስለሆነ በአስቸኳይ እንድከፈለን እንጠይቃለን።

12. ተቋርጦ የነበረዉ ጎንዮሽ የእድገት መሰላል እንድታስቀጥሉልን እንጠይቃለን ።

13. የተቋረጠዉን ከፍተኛ መሪ 1፣2፣3 ተግባራዊ በማድሰረግ ተመሳሳይ የአከፋፈል ስርአት እንድሮር እንድደረግ እንጠያቃለን።

14. እንደሚታወቀዉ የትምህርት ፍኖተ ካርታ ጥቅምም ጉዳትም አለዉ ነገር ግን ንቄት እስከሚመስል ድረስ ያሉትን መልካም አጋጣሚዎችን ማለትም የቲቶሪያል አበል፤የቤት አልዋንስ፤ገቃን ሶፍት ሳሙና፤ወዘተ ትቶ መመሪያ ቁጥር 02/2014 አዘጋግቶ ማቅረብ አላዋቂነት መሆኑን በመገንአብ መመሪያዉ እንድሻሻል እና ሁሉም ይቅማጥቅሞች ተግባራዊ እንድረግልን እንጠይቃለን።

15. የጤና መድህን በኢህ አመት ሰኔ ወር ላይ 3 ፐርሰንት ከደመወዝ ላይ እንደሚቆረጥ በተለያዩ ሚዲያዎች የተገለጸ ስለሆነ በፍኖተ ካርታዉ መሰረት የኛ የጤና ሽፍን በመንግስት የሚሸፈን ስለሆነ መንግስት ከወድሁ በማሰብ እራሱ እንድሸፍን በጥብቅ እናሳስባለን።

ግልባጭ

- ✓ ከክልል መምህራን ማህበር እስከ መሰረታዊ መምህራን ማህበር
- ✓ ከክልል ትምህርት ቢሮ እስከ ትምህርት ቤት

- ✓ ከክልል ምክር ቤት እስከ ቀበሌ ምክር ቤት
- ✓ ከክልል ብልጽግና ጽ/ቤት እስከ ወረዳ ብልጽግና ጽ/ቤት
- ✓ ለኢ.ሰ.መ.ጉ ከክልል እስከ ሚመለከተዉ ድረስ
- ✓ ለሁሉም መገናኛ ብዙሀን

ማሳሰቢያ ፡- ከላይ ያሉት ጥያቄዎች መልስ በፍጥነት የማያገኙ ከሆነ በህገ መንግስታችን አንቀጽ 30 መሰረት ከሰላማዊ ሰልፍ ጀምሮ እስከ ስራ ማቆም ህጉ በሚፈቅደዉ መሰረት ልንደርስ እንደምንችን ያለምንም ማቅማማት እያሳሰብን የሰብአዊ መብት ተከራካሪዎች አክቲቪስቶች ከጎናችን እንድትቆሙ እናሳስባለን።

የአማራ ክልል የመምህራን ህብረት